ከአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ አንድነት የተሠጠ መግለጫ

# የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ጉባዔ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣ በዓለም በዘፈቀደ ከታሠሩ ሰዎች ውስጥ አንዷ መሆናቸውን ይፋ አደረገ!

የኢትዮጵያ መንግሥት የወ/ት ብርቱካንን ዕስር በህግ መሠረት የተከናወነ ነው ቢልም በይቅርታ ህጉ መሠረት እንኳን እንዳልታሠረች ይታወቃል፡፡ ኢህአዴግ ወ/ት ብርቱካንን ያሰርኩት በህግ አግባብ ነው ብሎ ለማሳመን ጥረት ቢያደርግም ሌላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርና የገዛ አባላቱንም ማሳመን ፈጽሞ አልቻለም፡፡ ጥር 7 ቀን የወጣው የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ሪፖርት በዓለም ላይ በዘፈቀደ በዕስር ከሚማቅቁ ሰዎች ውስጥ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣ አንዷ መሆናቸው ይፋ አድርጓል፡፡

የወ/ት ብርቱካን እስር ህገ-ወጥ ብቻ ሣይሆን በዘፈቀደ የተደረገ መሆኑን በተባበሩት መንግሥታት ደረጃ በአጽንኦት መታወቁ ትልቅ ቁም ነገር ነው፡፡ ይህ እውቅና መንግሥት ብርቱካንን ያሠርኩት ህግና ሥርዓትን ተከትዬ ነው በማለት የዓለም አቀፍ ማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማሳሳት የሚያደርገው ሙከራ ከንቱ መቅረቱን ያሳያል፡፡ ነገር ግን ይህ የተባበሩት መንግሥታት እውቅና በራሱ ብቻውን በቂ አይሆንም፡፡ ስለዚህ የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ የኢትዮጵያ መንግሥት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣን በአስቸኳይ እንዲፈታ አበክሮ እንዲያሳስብ በዚህ አጋጣሚ እንጠይቃለን፡፡ በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚፈፀም ይህን መሠል ግፍና የዘፈቀደ እስር ለዓለም ሁሉ ሠላም ጠንቅ መሆኑን ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል፡፡ ሌሎች ዓለማቀፍ ተቋማትና መንግሥታትም ወ/ት ብርቱካንን ጨምሮ በሀገራችን በተለያዩ እስር ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የህሊና እስረኞች እንዲፈቱ ግፊታቸውን በኢትዮጵያ መንገሥት ላይ አጠናክረው እንዲቀጥሉ እናሳስባለን፡፡

የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ጉባኤ በዓለም የሰብዓዊ፣ የፖለቲካ፣ የሲቪል፣ የኢኮኖሚ፣ የባህል የልማት መብቶች ጥበቃ ያገኙ ዘንድ የሚታገልና ለዚህ እና ይህን ለመሠሉ ጉዳዮች የተቋቋመ አካል ነው፡፡ የኢህአዴግ መንግሥት ለእነዚህ እሴቶች ተገዥ ይሆን ዘንድ የመከታተል ኃላፊነትም በዚሁ አካል ላይ ወድቋል፡፡

ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘ ድፍን አስራ ስምንት ዓመት ሞልቶታል፡፡ በዚህ ረጅም የሥልጣን ዘመኑ ስለ ህግ የበላይነትና የሰብዓዊ መብት አያያዝ መቼም ከመለፈፍ ተቆጥቦ አያውቅም፡፡ ነገር ግን ተግባሩና ዲስኩሩ ፈጽሞ ሊጣጣሙ አልቻሉም፡፡ ይልቅስ ሀገራችን ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት

የሚፈፀምባት ግንባር ቀደም ሀገር በመሆን ትታወቃለች፡፡ ብዙ ማሳያዎችን መጥቀስ ቢቻልም የወ/ት ብርቱካን የእሥር ጉዳይ ብቻ እናንሳ፡፡ ሊቀመንበሯ የታሰሩት ከህግና ሥርዓት ውጭ ነው፡፡ ሊቀመንበሯን ለማሰብ ፓርቲያችን በተለያየ ጊዜ ለአዲስ አበባ መስተዳድር በመስቀል አደባባይ የሻማ ማብራት ሥነ-ሥርዓት ለማድረግ ተደጋጋሚ ጥያቄ ማቅረቡ ይታወቃል፡፡ መስተዳድሩ ግን ቀና ምላሽ ለመስጠት ፈጽሞ ፈቃደኛ ሊሆን አልቻለም፡፡ በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 30 መሠረት የተደነገገውን የዜጎች የመሰብሰብና ሃሳባቸውን የመግለጽ መብት በተደጋጋሚ በማንአለብኝነት እየተጣሰ ይገኛል፡፡ ይህ የሚያሳየው ኢህአዴግ በህገመንግሥቱ ላይ ያለማቋረጥ እያፌዘ መሆኑን ነው፡፡ የአዲስ አበባ መስተዳድርም በህገ መንግሥቱ ላይ ማመፁን በገሀድ እያሳየ ነው፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ በተለይ በምርጫ ዋዜማ በምንገኝበት በዚህ ወቅት የሰብዓዊ መብት ጥሰት በገዢው ፓርቲ በከፍተኛ ደረጃ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ሰሞኑን ህዩማን ራይትስ ዋች የተባለው ዓለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ድርጅት ይፋ ያደረገው ዘገባ ይህንን እውነታ ያረጋግጣል፡፡ እውነታው ይህ ቢሆንም ዓለማቀፍ ማህበረሰቡ ጥሰቱን በዝምታ እና በግዴለሽነት እያለፈው መሆኑ ደግሞ ችግሩን እጅግ የከፋ ያደርገዋል፡፡ እጅግም ያሳስበናል፡፡ ለምርጫ አራት ወር በቀረበት በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ሕዝባዊ ስብሰባ ጠርተን ራሳችንን የማስተዋወቅ መብታችንን እንኳን ተነፍገናል፡፡ በዚህ አገር አቤቱታ አቅርቦ መልስ የሚገኝበት ቦታ ጠፍቷል፡፡

ለ2002 ምርጫ እጩ ተወዳዳሪዎቻችን ለማቅረብ በከፍተኛ ዝግጅት ላይ ባለንበት በዚህ ወቅት ለተወዳዳሪነት የታሰቡ አባሎቻችንን እንደተለመደው በዘፈቀደ እለት እለት እየታሠሩ ይገኛሉ፡፡ ከዚያም በላይ በቅርቡ የፀደቀው የፀረ-ሽብር አዋጅ እየተጠቀሰባቸው በፍጥነት ተፈርዶባቸው ከምርጫ ጨዋታ ውጭ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው፡፡ መድረክ እና አባል ፓርቲዎቹ በሀገሪቱ ህግ እውቅና ያገኙ የምርጫ ፓርቲዎች ናቸው፡፡ የማይስማሙባቸው ህጎች ቢኖሩም ህግን አክብረው ለመሥራት እና ለመወዳደር ዝግጁነታቸውን ካሣወቁ ቆይተዋል፡፡ ይህም ሆኖ የሥነ-ምግባር ደንብ ፈራሚዎች አይደላችሁም በሚል ሰበብ አንድነትን ከጨዋታ ውጭ ለማድረግ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡ አንድነት የሀገሪቱን ህጎች አክብሮ እየሠራ የሚገኝ ፓርቲ ነው፡፡ ይህንን ተግባሩን ይቀጥልበታል፡፡ ከዚህ ውጭ ኢህአዴግ በፈጠረው ክለብ አልገባህም ተብሎ ህገ-መንግሥቱ ካጎናፀፈው መብቶችና ጥቅሞች እንዲገለል የሚደረገውን ዘመቻ አጥብቆ ያወግዛል፡፡ ህግን መሠረት አድርጎ ይህን ሀገወጥ ተግባርም ይታገላል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ምርጫው የፍላጎቱ እና የነፃነት ጥማቱ መግለጫ ይሆን ዘንድ በዚህ ምርጫ በነቂስ ወጥቶ እንዲመዘገብ እና እራሱን ለምርጫ እንዲያዘጋጅ እንጠይቃለን፡፡ ይህንን ሲያደርግ ለነፃነቱ የሚያደርገውን ትግል ዳር ለማድረስ አንድ እርምጃ ወደፊት ለመጓዝ ይችላል፡፡ በምርጫው በሙሣተፍ

ወ/ት ብርቱካንን ጨምሮ በፖለቲካ አስተሳሰባቸው ብቻ የታሠሩ ኢትዮጵያውንን እንዲያስብና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ በምርጫ ወቅት ኢህአዴግን አጥብቆ እንዲወተውት እንጠይቃለን፡፡

የተራበ፣ የተጠማ፣ እና በጭቆና ቀንበር ሥር እየማቀቀ የሚገኝ ሕዝብ መቸውንም ቢሆን ከፖለቲካው ሜደ እራሱን ለማራቅ በቂ ምክንያት ሊኖረው አይችልም፡፡ በሊቀመንበራችን በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣ ላይ እየተፈፀመ የሚገኘው ኢ-ሰብዓዊ እስር በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ እስር ተምሳሌት እንጂ የሊቀመንበሯ ብቻ አይደለም፡፡ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣ እስር በኢትጵያ ፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ መታፈን ገሃድነት ነው፡፡ እስከአሁን ዓለማቀፍ ማህበረሰቡ በወ/ት ብርቱካን ላይ እየተፈፀመ ያለውን እስርም ሆነ በአጠቃላይ የዴሞክራሲና የፍትሕ መታፈን እያየ እንዳላየ ማለፉ ለዴሞክራሲ እና ለሰብዓዊ መብት መከበር ያለውን ቁርጠኝነት ጉልህ የሆነ ጥያቄ ውስጥ ከቶታል፡፡

አንድነት የሠላማዊ ትግሉን አጠናክሮ በመቀጠል ሊቀመንበሯ እንዲፈቱ እንዲሁም በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ፀሐይ እንድትወጣ ያለማሰለስ ይታገላል፡፡ ለዚህም የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዲሁም የዓለማቀፍ ማህበረሰቡን ቁርጠኛ አጋርነት አጥብቆ ይጠይቃል፡፡

በዚህ አጋጣሚ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) የአየር መንገዳችን ንብረት በሆነው ቦይንግ 737-800 በበረራ ቁጥር 409 ከበይሩት ወደ አዲስ አበባ ሲበሩ በነበሩ ኢትጵያውያን የአየር መንገዱ ሠራተኞችና ተሳፋሪዎች እንዲሁም በበረራው ውስጥ የነበሩ የውጭ ሀገራት ዜጎች ላይ የደረሰውን ለአዕምሮ እጅግ የከበደ የሰቆቃ ዜና የሰማው እጅግ ከፍ ባለ ሀዘንና ድንጋጤ ነው፡፡ ለተጎጅዎቹ ቤተሠቦች እና ለመለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ልባዊ መጽናናት ይመኛል፡፡

አንድነት ፓርቲ በዚህ ድንገተኛ መሪር ሃዘን ውስጥ ለሚገኙ የሠለባዎቹ ቤተሠቦችና የቅርብ ወዳጆች የአየር መንገዱ ሠራተኞች እንዲሁም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ልባዊ መጽናናትን ይመኛል፡፡ እንዲሁም አየር መንገዳችን ያጋጠመውን እጅግ አሳዛኝ አደጋና ሃዘን ተቋቁሞ ከዚህ በፊት የነበረውን ስመ ጥር አየር መንገድነቱንና የአገራችን አርማነቱን ከመቸውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ አጠናክሮ እንዲቀጥል አንድነት ፓርቲ ከልብ ይመኛል፡፡ አየር መንገዳችን ተጠናክሮ እንደሚወጣም እምነታችን ከፍ ያለ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ አንድነት

ጥር 20 ቀን 2002 ዓም

አዲስ አበባ